የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)
*Ethiopian People´s Revolutionry Party(EPRP*

ሰኔ 6 ቀን 2005 ዓ.ም.

ለዘሐበሻ ድረ ገጽ አዘጋጆች
ሚኒያፖሊስ ሚኒሶታ

**<u>"ኢሕአፓ በአዲስ አበባ በርካታ ቦታዎች በህቡዕ ወረቀት በተነኩ አለ"</u>** በሚል ርእስ በፎቶሾፕ የማታለያ ዘዴ የተዘጋጀ ፎቶግራፍን አዝሎ በድረገጻችሁ ላይ ያወጣችሁት መግለጫ ኢሕአፓን የማይመለከት መሆኑን ልናሳውቃችሁ እንወዳለን። የኢሕአፓ ህልውናና እንቅስቃሴ የማይጥማቸውና የሚያቃጥላቸው በወያኔ ውስጥ ያሉም ሆነ ከዚያ ውጭ ያሉ ቡድኖችና ግለሰቦች ሕዝብን ውዥንብር ውስጥ ልንጥል እንችላለን፤ ኢሕአፓን እናሳጣለን ከሚል ቅዠት ይህን ዓይነት መግለጫ ማውጣታቸውን የምንጠብቀው ቢሆንም የዚህ ድረገጽ አዘጋጆች በዚህ ላይ ተባባሪ መሆናችሁ ግን ግልጽ ሊሆንልን አልቻለም።

ከዚህ በፊትም በኢሕአፖና በኢሕአፓ ወጣቶች ክንፍ ድርጅት ስም በጸረ ኢሕአፓ ግለሰቦች የተዘጋጁ የሀሰት መግለጫዎች መውጣቸውን ተቃውሞ ብናሰማም የድረ ገጹ አዘጋጆች ተቃውሟችንን ችላ በማለት የተለያዩ መግለጫዎችን ስታወጡ መቆየታችሁ ይታወቃል። ይህ የውዥንብር መግለጫ ባስቸኳይ ከድረ ገጻችሁ ላይ እንዲነሳ እየጠየቅን ወደፊትም ተመሳሳይ ጸረ ኢሕአፓ የሆነ ግለሰቦች የሚያወጡትን ውዥንብሮች በድረ ገጻችሁ ላይ ከማስተናገድ እንድትቆጠቡ እናሳስባለን።

የኢሕአፓ ጽ/ቤት

ዋሽንግተን ዲሲ

**EPRP**
**P.O.BOX 73337**
**Washington DC, 20056**
**USA**

**Email [ESPIC@aol.com](mailto:ESPIC@aol.com)**
**Website [WWW.EPRP.com](http://WWW.EPRP.com)**

**EPRP**
**BP 2**
**92270 Bois Colombes**
**France**

**Tel. 202 291 4217 Fax: 202 291 7645**